ነሐሴ 24 ቀን 2006 ዓ/ም

ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

የካ ምድብ ፍ/ብሔር ችሎት

አዲስ አበባ

ከሳሽ፡- ወ/ሮ

አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 01

ተከሳሽ፡- አቶ

አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤ.ቁ.143

ከሳሽ በነሐሴ **07** ቀን **2006** ዓ/ም ፅፋ ላቀረበቸው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ**. 234** መሠረት የተሠጠ መልስ ነው።

**1.** የክሱ ዝርዝር ባጭሩ

1.1 ከሳሽ በነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ/ም ተከሳሽ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ቀበሌ 01/02 የ.ቤ.ቁ. 298 ተመዝግቦ የሚገኝ ባለ አንድ ክፍል መኖሪያ ቤት ቀበሌ በህጋዊ መንገድ ያሸገውን ቤትን ግድግዳውን ከኋላ በመቅደድ ከተከራየው የቀበሌ ቤት ጋር በመቀላቀል ህገወጥ በሆነ መንገድ ቤቱን ይዞ ይገኛል።

1.2 ተከሳሽ ቤቱን ለቆ እንዲወጣ በቀበሌ አስተዳደር ጭምር ቢጠየቅም ፈቃደኛ መሆን አልቻለም በማለት ክስ አቅርባለች።

**2.** ከተከሳሽ የተሠጠ መልስ ባጭሩ

2.1 ተከሳሽ በአሁን ሰዓት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ቀበሌ 01/02 የ.ቤ.ቁ. 298 የምኖርበት የከሳሽ የቤተሰቦቿ ቤት ሲሆን በ 1967 ዓ/ም በደርግ ጊዜ ከቤተሰቦቿ መንግስት ወርሶባቸው በ 1987 ዓ/ም በየካ ክ/ከተማ የቀድሞ ቀበሌ 06 መስተዳደር ህጋዊ ውል በማስፈረም በህጋዊ መልኩ 1 ክፍል ኩሽና እና ሽንት ቤት ጨምሮ ለተከሳሽ አከራይቶኛል።

2.2 ከሳሽ ቀበሌ ያሸገውን ግድግዳ ከኋላ በመቅደድ ከተከራየው ቤት ጋር በህገወጥ መልኩ ቀላቅሎታል ብላ የገለፀቸው መኖሪያ ቤት ቀበሌውም መጥቶ ያላሸገው እና ቤተሰቦቿ በህይወት እያሉ በሽያጭ ለ 3 ኛ ወገን ያስተላለፉት መኖሪያ ቤት ነው።

2.3 ተከሳሽ ቤቱን ለቆ እንዲወጣ በቀበሌ አስተዳደር ጭምር ቢጠየቅም ፈቃደኛ ሊሆን አልቻለም በማለት ክስ አቅርባለች ነገር ግን የየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02 መስተዳደር በህጋዊ መልኩ ውል አፈራርሞኝ በየወሩ ኪራይ እየከፈልኩ የምገኝ ሲሆን ምንም አይነት ቤቱን ለቅቄ እንድወጣ ከቀበሌው የመጣ ትዕዛዝ የለም።

**3.** ከሳሽ ከተከበረው ፍ/ቤት የምጠይቀው ዳኝነት

3.1 ከሳሽ በሀሰት እና በተንኮል ሆን ብላ እኔን ለማንገላታት ያደረገችው እና ተከሳሽም በህጋዊ መልኩ በውል የቀበሌ ቤቱን ከመንግስት የተከራየሁ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጎ እንዲያሰናብተኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

3.2 ተከሳሽ ከዚህ ክስ ጋር ያወጣሁት ወጪና ኪሣራ ከሳሽ እንድትከፍለኝ ፍ/ቤቱ በቁርጥ እንዲወስንልኝ።

ከላይ የቀረበው እውነት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሠረት አረጋግጣለሁ።

ተከሳሽ

ነሐሴ 24 ቀን 2006 ዓ/ም

ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

የካ ምድብ ፍ/ብሔር ችሎት

አዲስ አበባ

ከሳሽ፡- ወ/ሮ

አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 01

ተከሳሽ፡- አቶ

አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤ.ቁ.143

<u>በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. **223** መሠረት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ።</u>

**1.** የሰነድ ማስረጃ

1.1 በ 1987 ዓ/ም የየካ ክ/ከተማ የቀድሞ 06 የአሁኑ ወረዳ 01 ቀበሌ 01/02 የቤት ኪራይ ውል ያስፈረመኝ እና በየዓመቱ የፈረምኩበት እና የሞላሁበት ቅፆች ---------------------

1.2 ከ 1987 ዓ/ም ጀምሮ የቤት ኪራይ ውል በቀበሌ የተከፈለበት ደረሰኞች በድምሩ ------------- ገፅ ኮፒ ዋናው በተከሳሽ እጅ የሚገኝ።

**2.** <u>የሠው ምስክሮች</u>

ተከሳሽ የቀበሌ መኖሪያ ቤቱን በህጋዊ መንገድ እንደተከራየሁ የሚያስረዱልኝ፡-

1. አ አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ
2. አቶ አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ
3. ወ/ሮ አድራሻ፡- አ/አ የካ ክ/ከተማ

ጭብጡ ካልተለወጠ ወይም ፍ/ቤቱ ካላዘዘ በቀር ያሉኝ ማስረጃዎች ከላይ የተገለፁት ናቸው።

ተከሳሽ

አቶ ገ/ሚካኤል አዩ